# የህዳሴው ግድብ አሁን ያለበት ደረጃ ሲቃኝ

**ለይኩን ዘለዓለም 1/15/14**

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዓባይ ላይ ቤት ሰርቶ የሀገር ሲሳይ የሚሆንበት ዘመን ያበሰረ ያበሰረ በመሆኑ ለዘመናት ሲቆጭና ከንፈሩን ሲመጥ ለዘለቀው ኢትዮጵያዊ ደስታን የፈጠረ፣ ለሀገራችን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዘንድም ታላቅ ተስፋን ያጫረ ነው፡፡ እርግጥም ይህ የህዝብ ሃብት የዘመናት ምኞታቸውን እንደሚያሳካ የተማመኑ ዜጎች የየራሳቸውን ስያሜ ሲሰጡት ማስተዋል የተለመደ ጉዳይ እየሆነ ነው። አንዳንዶች የባንዴራው ፕሮጀክት ሲሉት፣ ሌሎቹ ደግሞ የዘመኑ ስጦታ ይሉታል፡፡ሌላ...ሌላም...፡፡ ያም ሆነ ይህ ስያሜውን ዘርዝረን ስለማንዘልቀው "ስመ ብዙ" ብለን ብናልፈው የተሻለ ይመስለኛል።

በነገራችን ላይ ዛሬ...ዛሬ እየቀረ ሄደ እንጂ ወደ እዚህ ዓለም ለተቀላቀለ ህጻን በቤተ-ዘመድ ዘንድ ስም ማውጣት የተለመደ እንደነበር የዕድሜ ባለጸጎች ያወሳሉ፡፡ በቤት ስም፣ በቅፅል ስም፣ በቤተዘመድ ስም፣ በሃይማኖት ስም... ወዘተ. መጠራት ይዘወተር እንደነበርም እንዲሁ፡፡ ያም ሆኖ ግን ህጻኑ እያደገ ሲሄድ የሚኖረው ስም አንድ ብቻ ይሆናል፡፡ እናም መላው ኢትዮጵያውያን ከድህነት አረንቋ የመውጣት ጥረት ውጤት የሆነውና ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ለስኬቱ የሚረባረቡለት ታላቁ የህዳሴ ግድብ "ስመ ብዙ" መሆን ሲያንሰው እንጂ የሚበዛበት አይደለም፡፡ ሁሉም የሀገራችን ህዝብ በስስት የሚመለከተው ነውና።

እንደሚታወቀው እኛ ኢትዮጵያውያን ለሰንደቅ ዓላማችን የምንሰጠው ክብር ከማንም በላይ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ሰንደቅ ዓላማችን ሁሉም ነገራችን መሆኑን እንኳንስ ወዳጅ ጠላትም የሚመሰክርልን ሃቅ ነውና፡፡ ለምን ቢባል የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስከበር ቀፎው እንደተነካ ንብ የተመሙበት የትናንት በስቲያው አድዋ፣ የትናንቱ የፀረ-ሻዕቢያው ትግል፣ በየስፖርት አደባባዩ የሚደምቀው ሰንደቅ ዓላማ የዚህ እውነታ አስረጅ ስለሆነ ነው፡፡ የዘመናት ቁጭትን ለሻረው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ብስራት ዜና ማጀቢያነት በግምባር ቀደምትነት መዋሉ ሳይዘነጋ ማለቴ ነው፡፡

ታዲያ “የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ” ፕሮጀክት ብለው የሰየሙት ይሁኑ “የዘመኑ ስጦታ” ያሉት ወገኖች ፕሮጀክቱ የመላው ኢትዮጵያውያን አሻራቸውን ያሳረፉበት የማንነታቸው መገለጫ እንደሆነ ጠንቅቀው የሚያውቁና ይገልፅልናል ባሉት ስያሜ መጥራታቸው የሚያከራ ነው፡፡ ለማንኛውም ግን በዋና መጠሪያው “ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ” የሀገራችን ህዳሴ ማብሰሪያ የማንነታችን አሻራ መገለጫ ሆኖ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ እኔም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አሁን የሚገኝበትን ሁኔታ ላስቃኛችሁ ወደድኩ። እናም ትናንትን በስሱ እየዳሰስኩ ዛሬ የሚገኝበትን ሁኔታ እነሆ እላለሁ፡፡ መልካም ንባብ።…

“ዛሬ የትናንት ውጤት ነው” እንዲሉ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ስናነሳ ወደ አእምሯችን የሚመጣው “ባለቤቶቹ እኛ፣ መሃንዲሱ እኛው፣ ግንበኞች እኛው…” የሚለው የታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ ንግግር ነው ቢባል ሁሉን የሚያስማማ ይመስለኛል፡፡ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ መጋቢት 24 ቀን 2004 ዓ.ም የመሠረት ድንጋይ የማኖር ሥነ- ሥርዓትን ተከትሎ በኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዘንድ የተንጸባረቀው ስሜትም እንዲሁ፡፡

ቀስቃሽና ቆስቋሽ ሳያስፈልገው፣ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ጾታና ዕድሜ ሳይገድበው የምንጊዜውም የማንነቱ መገለጫ በሆነው ሰንደቅ ዓላማው ደምቆ ወደየአደባባዩ የተመመው መላው ኢትዮጵያዊ “ባለቤቱ እሱ፣ መሃንዲሱ ራሱ፣ ግምበኛው እርሱ…” የመሆኑን እውነታ ምላሽ የሰጠበት ሂደትም መቼም የሚዘነጋ አይሆንም፡፡ በዚህም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለመገንባት ያለውን ቁርጠኝነት የ“ይቻላል” ምላሹን በመስጠት ታሪክ የማይዘነጋው ተግባር አከናውኗል፡፡

እንደሚታወቀው የግድቡ ግንባታ በበርካታ ክስተቶች የተሞላ ነው። በተለይም ለዘመናት አብሮን የዘለቀው ዓባይን የመገደብ አይሞከሬነት አስተሳሰብ ያከተመበትና የ“ይቻላል” አስተሳሰብ ለውጥ የተፈጠረበት፣ በየትኛውም የዓለማችን ክፍል የሚገኝ ኢትዮጵያዊ የዜግነት ድርሻውን ለመወጣት ቃል የገባበት እንዲሁም ምላሹን የሰጠበት ፕሮጀክት መሆኑ በዓለማችን በዜጎች ገንዘብና ባለቤትነት የሚገነባ ብቸኛው ፕሮጀክት መሆኑ ከፕሮጀክቱ ክስተቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ አዎ! ዛሬ የግድቡ መሰረተ ድንጋይ ከተጣለ ወደ ሁለተኛ ዓመቱ እየተቃረብን ነው፡፡ ታዲያ የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ስራው በተፈለገው

ሁኔታና ፍጥነት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ግንባታው የተጀመረው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለዘመናት ጥቅም ሳይሰጥ የቆየው የዓባይ ወንዝ ኢትዮጵያን ለቆ ከሚወጣበት ከሃያ እስከ አርባ ኪሎ ሜትር መካከል ላይ እየተገነባ ይገኛል፡፡

ግንባታው በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ባካበተው የሳሊኒ ኮንስትራክሽን ኩባንያና በሀገር በቀሉ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን አማካኝነት እየተከናወነ ሲሆን፤ የመጀመሪያው ምዕራፍ ተጠናቆ ዋነኛ የግንባታ ሥራው በመፋጠን ላይ ነው፡፡ የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ አንድ ሺህ 780 ሜትር ርዝመትና 145 ሜትር ከፍታ እንደሚኖረው የሚነገርለት የህዳሴው ግድብ ግንባታ፤ የሲቪል ሥራ የሚከናወነው በሳሊኒ ኮንስትራክሽን፣ የኤሌክትሮ እና የሃይድሮ ሜካኒካል ሥራው በብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን፣ የማማከሩ ተግባር ደግሞ የጣልያንና የፈረንሳይ መሃንዲሶች ጥምር ኩባንያ አማካኝነት እየተካሄደ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ አስተማማኝና ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

የግድብ ግንባታ ሥራ የተለያዩ ምዕራፎችን የሚያካትትና ደረጃ በደረጃ የሚከናወን መሆኑን የዘርፉ ሙያተኞች ያስረዳሉ፡፡ የቦታ ጥናት (Site Testing) የግድቡ አይነት (design) ቦታ ማዘጋጀት (Site preparation) የግድብ ሥራ (dam construction) ዋና ዋና ምዕራፎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሥራ ከላይ የተጠቀሱትን ምዕራፎች በተገቢው መልኩ አልፎ ዛሬ ላይ ወደ ዋነኛ ግንባታ ሥራ መሸጋገር ችሏል፡፡

ከዚህ አኳያ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የመጀመሪያው ምዕራፍ የሆነው የዲዛይን ሥራ ተጠናቆ ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ ማለትም የግድብ ሥራው ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ውጤታማ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ከነዚህ ተግባራት መካከልም የሥራው አንዱ ክፍል የሆነው የወንዙን ተፈጥሯዊ የፍሰት አቅጣጫ የማስቀየር ሥራ ይገኝበታል፡፡ የግድቡ ሥራን በተፈለገው ፍጥነት ለማከናውን ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው የወንዙን ተፈጥሯዊ የፍሰት አቅጣጫ የማስቀየሩ ሥራም በተፈለገው ሁኔታ ማሳካት በመቻሉ የመጀመሪያውና የግንባታው ስኬታማነትን ያረጋገጠ ተግባር እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

የግንባታውን ሥራ በተጀመረበት አንደኛ ዓመትን በታላቅ ደስታና ሀገራዊ ኩራት ማክበር ያስቻለው የወንዙን አቅጣጫ የማስቀየር ስራው በስኬታማነት መጠናቀቅ ወደ ሚቀጥለውና ዋናው የግድቡ ግንባታ ሥራ መሸጋገርን ከማብሰሩም ባሻገር፤ የፀረ-ድህነት ትግሉ በትክክለኛው መንገድ ላይ እየተጓዘ እንደሆነም የትናንት ትዝታችን ነበር፡፡ ታዲያ "ነገርን ነገር ያነሳዋል" እንዲሉ የግድብ ግንባታን ስናነሳ የዓላማችን ሃያሏ ሀገር አሜሪካ በ1930ዎቹ ያስገነባቸው የሁቨር ግድብ ይጠቀሳል፡፡ በኮሎራዶ ወንዝ ላይ የተገነባው የሁቨር ግድብ አሜሪካውያኑ ግሬት ዲፕረሽን ብለው በሚጠሩት አስቸጋሪ ወቅት ከተገነቡት ግድቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ በወቅቱ የግድቡ ግንባታ የዕድገታቸው ዋነኛ መሰረት እንደሆነ በማሰብ በዜጎች ከፍተኛ መነሳሳትን የፈጠረ እንደነበርም አይዘነጋም፡፡ የግድቡ ግንባታ ሥራ ለዜጎች ከፍተኛ የስራ ዕድል መፍጠር መቻሉም እንዲሁ፡፡ በዚህም ለግድቡ የአርማታ ሥራ ብቻ 5000 ሺህ የሀገሪቱ ዜጎች ተሰማርተው ኑሯቸውን ለመግፋት አስችሏቸዋል፡፡ የሁቨር ግድብ ግንባታ ሥራ የከሎራዶ ወንዝን ተፈጥሯዊ የፍሰት አቅጣጫ ለማስቀየር ከአንድ ዓመት በላይ መፍጀቱንም ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ታዲያ በዚህ እውነታ የምንረዳው ነገር ቢኖር የሁቨር ግድብ በበርካታ ጉዳዮች ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም የሚለይበት ሁኔታ መኖሩንም ጭምር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የወንዙን የፍሰት አቅጣጫ ለመቀየር የፈጀው ጊዜና ፍጥነት ከወንዙ መጠን ጋር ተዳምሮ ግድቡ በተፋጠነ መልክ እንዲከናወን ማድረጉ ተጠቃሽ ሲሆን፤ ይህም የስኬታማነቱን ደረጃ ፈጣንነት የሚያመላክት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከፍተኛ ተስፋ የሰነቁበት፣ የዘመናት የቁጭት እንባቸው የታበሰበት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሥራ የወንዙን የፍሰት አቅጣጫ መቀየርን ተከትሎ በተካሄደው ቅንጅታዊ ሥራ ከፍተኛ ለውጥን በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም አጠቃላይ የግንባታ ሂደቱ 30 በመቶ ሊደርስ ችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ አንዳንድ የሙባረክ አገዛዝ ዘመን ኋላ ቀር አስተሳሰብ የተጠናወታቸው የግብፅ ባለስልጣነት "የግድቡ ግንባታ 30 በመቶ ደርሷል የሚባለው ለፖለቲካ ትርፍ ፍጆታ ነው" በማለት የሚያስወሩት አሉባልታ መሰረተ-ቢስ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም። መሬት ላይ ያለው ዕውነታ ይኸው ነውና። ያም ሆነ ይህ ግን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የግንባታ ሥራ የተለያዩ

ክንዋኔዎችን ያካተተ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተለያዩ የግንባታ መሣሪያዎችና ግብዓትን የሚጠይቅ በመሆኑ አስፈላጊው ሁሉ እንዲሟላ ተደርጓል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የግድቡን ሥራ ለማፋጠን የሚያስችሉ ከ1600 በላይ ከፍተኛ ማሽነሪዎች በስፍራው ይገኛሉ፡፡ ሃያ አራት ሰዓታት ያለማቋረጥ እየተገነባ በሚገኘው የህዳሴው ግድብ ከ6 ሺህ 600 የሚበልጡ ሰራተኞችም በሥራው ላይ ተሰማርተው በከፍተኛ ሀገራዊ ስሜትና ኃላፊነት ተግባራቸውን በሀገራዊ ፍቅር ስሜት በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ በዚህም የግንባታ ሥራው በመለዋወጫና ግብዓት ረገድ አንዳች ችግር ሳይገጥመው በተፈለገው ፍጥነት እንዲጓዝ አስችሎታል፡፡

በአሁኑ ወቅት የዋናው ግድብ (main dam) የቁፋሮ ሥራ በመካሄድ ላይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የግድቡ ግንባታ ሥራም ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው የመሬት ክፍል የሮለር ኮምፓክትድ ኮንክሬት ሙሌት ሥራ ተጀምሮ በመፋጠን ላይ ይገኛል፡፡ ሌላውና የግንባታው አካል የሆነው መለስተኛ ቁመት ማለትም 50 ሜትር ቁመትና 5 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውና “ሳደንደም” በሚል ስያሜ የሚታወቀው የግድቡ ሥራም ውኃው የሚተኛበት ግግር ድንጋይ በመገኘቱ የአሰፋልት ኮንክሪት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ሀገር በቀሉ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፓሬሽንም የቦክስ ካልበርት ተከላ ሥራውን ጀምሯል። ሌላውና የግድቡ ግንባታ ሥራ የኃይል ማመንጫ ግንባታ ነው፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለት የኃይል ማመንጫዎች አሉት፡፡ የኃይል ማመንጫዎቹ የሚገኙት በግድቡ የቀኝና የግራ ክፍል ሲሆን፣ ሁለቱም አስራ ስድስት ዩኒቶች ይኖሩታል፡፡ በመሆኑም አስር ዩኒቶችን ያቀፈው የቀኙ ክፍል እንዲሁም ስድስት ዩኒቶች ያሉት የበስተግራ በኩል የሚገኘው የኃይል ማመንጫ እያንዳንዱ ዩኒቶች 375 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያላቸው ናቸው። የቁፋሮ ስራው በመካሄድ ላይ ከመሆኑ በተጨማሪ የአርማታ ሙሌትም በቅርቡ እንደሚጀመር ነው መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡

ሌላው በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እየተከናወነ ያለው ሥራ የኤሌትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ግንባታ ነው፡፡ ሥራው ሲጠናቀቅ ማከፋፈያው በሀገራችን ትልቁ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ባለ 500 ኪሎ ቮልት የኤሌትሪክ ማከፋፈያው በሀገራችን የመጀመሪያው ትልቁ ቮልቴጅ ከመሆኑም ባሻገር የኃይል መቆራረጥን በማስገድ ረገድም ሚናው የላቀ ነው፡፡ ይህም የሀገራችን የኃይል ማከፋፈያ የዕድገት ደረጃን ማሳደግ የሚችል ይሆናል፡፡

የፕሮጀክቱ ሌላኛው ስትራክቸር ስፒል ዌይ ይሰኛል፡፡ በዚህ ስር የሚከናወነውን ሥራ በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው መክፈቻና መዝጊያ በሮች ያሉት የስፒል ዌይ ስራ ነው፡፡ ይህ ሥራ የመጀመሪያው ምዕራፍ ተጠናቆ ወደ ሁለተኛው ተግባራዊ ሥራ ለመሸጋገር በዝግጅት ላይ እንደሆነ ከስፍራው የተገኙ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ሁለተኛው በር የሌለው የውኃ ማስተንፈሻ ሥራ ነው፡፡ የዚህ የግንባታ ሥራም በመካሄድ ይገኛል፡፡ የማስተንፈሻው ዓላማ ግድቡ በሚሞላበት ጊዜና የውኃው መጠን ከፍተኛ ሲሆን ለመቀነስ የሚረዳ ነው። ይህ ሥራም የመጀመሪያው ምዕራፍ ተጠናቋል፡፡

ሌላው ኢመርጀንሲ ሲፒል ዌይ የሚባለው ስትራክቸር ሥራ ሲሆን፤ ጥናቱ ተጠናቆ የግንባታ ሥራው በመካሄድ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክቱ በተፈለገው መንገድና በተፋጠነ ሁኔታ እየተካሄደ የሚገኝ ለመሆኑ በመከናወን ላይ የሚገኙት ተግባራት በማሳያነት መጥቀሱ ለእውነታነቱ ከበቂ በላይ ይሆናል፡፡

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሥራ በተለይም የወንዙ ተፈጥሯዊ የፍሰት አቅጣጫን በተሳካ ሁኔታ ማስቀየር ከተቻለ በኋላ ያለምንም ዕረፍት ለመስራት በተደረገው ሁለንተናዊ ጥረት ከፍተኛ ዕድገት ማሳየት ችሏል፡፡ በግንባታ ሥራው ሲቪል ሥራዎች ላይ የተሰማራው ሳሊኒ ኮንስትራክሽን የቁፋሮ፣ የአርማታ ሙሌትና ተዛማጅ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ማሽነሪዎች ያሉት ሲሆን፤ በሰዓት ሁለት ሺህ ቶን ጠጠር በሚፈጭና በሰዓት 400 ሜትር ኩዮብ በሚያመርቱ ሁለት ፕላንቶች እየታገዘ የግንባታ ሥራውን በታለመለት ሁኔታ እንዲጓዝ እያደረገ ነው፡፡

ሀገር በቀሉ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በበኩሉ የኤሌክትሮ ሚካኒካልና የሃይድሮ ሜካኒካል እንዲሁም ተዛማጅ የመቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ዲዛይን የማድረግ፣ የመፈብረክ፣ የማምረት፣ የመትከልና ፈትሾ የማስረከብ ስራውን በተገቢው ሁኔታ በመፈጸም አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ሀገራዊ አቅምን በማጠናከር ረገድ ትልቅ አቅም እየፈጠረ በመምጣቱ፤ በዘርፉ ለሚካሄድ የግንባታ ሥራ ራስን በመቻል ረገድ ከፍተኛ ዕድል እየፈጠረ መሆኑ በገሃድ ያሳያል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የተለያዩ ሁነቶችን ተሻግሮ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ በዚህም የግንባታ ሥራውን ከጋራ ተጠቃሚነት አኳያ በመመዘን ድጋፋቸውን ያንጸባረቁ ሀገሮች የተስተዋሉበት እንዲሁም ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀም ከምንጊዜውም በላይ ትኩረት እንዲስብ አስችሏል። በተቃራኒው ደግሞ ሥራውን ከመቃወም እስከ የማደናቀፍ ሴራ ጥንስስም ታይቶበታል፡፡ ነገር ግን መንግስትና ህዝብ በሰጡት ትኩረት የግንባታ ሥራው ላፍታም ሳይደናቀፍ በታለመለት መንገድ እየተፈጸመ አሁን በሚገኝበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ለዚህም በመላው ኢትዮጵያዊ የተፈጠረው መነሳሳትና የመንግስት የፀረ- ድህነት ትግል ቁርጠኝነት ለግንባታ ሥራው የእስካሁኑ ጉዞ ስኬታማነት በምክንያት የሚጠቀሱ ዋና ዋና ጉዳዮች ናቸው፡፡

ሀገራዊው ቀደሚ አጀንዳ የሆነው የግድቡ ሥራ በአሁኑ ጊዜም የቅርብ ክትትል አልተለየውም፡፡ መላው የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደ “ዓይን ብሌናቸው” የሚንከባከቡት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በየዕለቱ በርካታ ዜጎች ይጎበኙታል፡፡ ይህም በሥራው ለተሰማሩ ኢትዮጵያውያንና የውጭ ዜጎች ትልቅ የሞራል ስንቅ በመሆኑ ለሥራው መፋጠን ሚናው የላቀ ሆኗል፡፡

በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሥራ በርካታ ጠቀሜታዎችን ያጎናጸፈ ነው፡፡ በተለይ የስራ ዕድልን ከመፍጠር አኳያ በአሁኑ ጊዜ በስራው ላይ ከተሰማሩት ከ6 ሺህ 600 የሚበልጡ ሠራተኞች ውስጥ የውጭ ዜጎች 550 ብቻ መሆናቸው ከ6000 የሚበልጡ ኢትዮጵያውያንን የዕድሉ ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል፡፡

ይህም ሀገራዊና ግለሰባዊ ፋይዳው ምን ያህል እንደሆነ መገመቱ የሚከብድ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም እንደ ግለሰብ የገቢ ማስገኛ ከመሆኑ ባሻገር፣ የዕውቀት መቅሰሚያ መንገድ በመሆኑ የነገን ብሩህነት ማመላከት ያስችላል፡፡ በተለይም የዓለማችን ከተፈጥሮ ጋር የሚስማማ የኃይል ፍላጎትን የሚያሟላው የሃይድሮ ኃይል ማመንጫ ግንባታ ሥራ መስፋፋት ጋር ተያይዞ በዘርፉ ተሰማርቶ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል በመሆኑ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

በሌላም በኩል በሀገራችን በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ለሚገኘው የመሠረተ ልማት ግንባታ ምላሽ የሚሰጥ የሰው ኃይል መፈጠሩ ሀገራዊ ፋይዳው የላቀ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለማመን በሚያዳግት ሁኔታ እያስገመገመ ለመጣው የኢንቨስትመንት ፍሰት በቂ ምላሽ መስጠት የሚችል የኃይል አቅርቦት የሚያጎናጽፍ በመሆኑ፤ ለሀገራዊው ዕድገት ቀጣይነት ታላቅ ዋስትና እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡

የግድቡ ጠቀሜታ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ከጎረቤት ሀገሮች ጋርም ኢኮኖሚያዊ ትስስራችንን ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋግራል፡፡ ይህም ለአካባቢው ሀገራት የጋራ ዕድገትና አስተማማኝ ሠላም መስፈን አስተዋጽኦው የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም በጀርባችን ላይ የተፈናጠጠው ድህነትን አሽቀንጥረን ለመጣል ለጀመርነው የፀረ-ድህነት ትግል ከግብ መድረስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። እርግጥም የግድቡ ግንባታ ሥራ ፅናትና ቁርጠኝነት በተሞላበት ሁኔታ በመካሄድ ላይ መሆኑን ለሚመለከተው ሰው የሚያጎናፅፈው ሀገራዊ ኩራት ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም፡፡

አዎ! የነገዋን ኢትዮጵያ የሚያመላክተው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሥራ መሠረተ ድንጋይ ከማኖር ጀምሮ መላው ኢትዮጵያዊ የሰጠው ምላሽ ለስኬታማነቱ በር መከፈት ከፍተኛ ድርሻ እንደነበረው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ በወቅቱ በመላው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተፈጠረው መነሳሳት በተለይ ለግድቡ ግንባታ መጀመር ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ ህልፈተ- ህይወት በኋላም "እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን" የሚል ቃል በመግባት ግለቱን ጠብቆ በመጓዝ ላይ ይገኛል፡፡ እርሳቸው እንዳሉትም የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ "ባለቤቱ እኛው፣ ግንበኛውም እኛ፣ መሃንዲሱም እኛው..." በመሆን ለሀገራዊው ልማታችን ምላሽ የሚሰጠውን ግድብ ማፋጠን መቻላችን ለፀረ - ድህነት ትግሉ ከግብ መድረስ ያለንን ቁርጠኝነት የሚያመላክት ተግባር ነው፡፡

ታዲያ ለግድቡ ግንባታ ስኬታማነት እየተካሄደ ያለው ሁለንተናዊ ጥረትና መላው ኢትዮጵያዊ ዜጋ እያሳየው የሚገኘው ቁርጠኝነትና ጽናት የተሞለበት ተግባር ዋነኛው ምክንያት የግድቡን ፋይዳ የሚገነዘብ፣ የነገዋን ኢትዮጵያ አርቆ የሚመለከትና የለውጥ ኃይል በመፈጠሩ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ በመሆኑም ይህ ሀገራዊ ጥንካሬ ግለቱን ጠብቆ የሚጓዝ በመሆኑ የታላቁ

የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሥራ እንደ አጀማመሩ ሁሉ ፍጻሜውም ያማረ እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይሆንም፡፡

እርግጥም ወልዶ መሳምንና ዘርቶ መቃምን የማይመኝ ሰው ይኖራል ተብሎ ስለማይታሰብ የታላቁ ህዳሴ ግድብ “ባለቤቶቹ እኛ፣ መሃንዲሱ እኛው፣ ግንበኞቹ…” መሆናችንን እያስመሰከርን ለመጣንለት የታላቁ ህዳሴ ግድባችን በስኬት መቋጨት የ“እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን” ቃላችንን በመጠበቅ ዛሬም እንደ ከትናንቱ በበለጠ ሁኔታ በግድቡ ዙሪያ ተሰባስበን የህዳሴያችንን ጥርጊያ መንገድ ይበልጥ መክፈት ይኖርብናል። በተለይም የሀገራችንን ዕድገት የማይሹ የውስጥም ይሁን የውጭ ሃይሎችን ውዥንብር ወደ ጎን በማለት በተግባራዊው የግድቡ ሥራ ላይ መረባረብን ለነገ መተው የለብንም። “ውሾቹ ይጮሃሉ፣ ግመሎቹ ግን ጉዟቸውን ቀጥለዋል” የሚለውን አባባል ሁሌም ማስታወስ የእኛው፣ የህዳሴው ባለቤቶች የሰርክ ተግባር መሆኑን ልንዘነጋው አይገባም። አበቃሁ።